# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 13

ሚያዝያ 2 ቀን 2014ዓም( 10-04-2022)

የዛሬውም አገር እንዴት ሰነበተች ጥንቅራችን እንዳለፉት ጊዜያቶች በአስከፊ ዜናዎች የታጨቀ ይሆናል። አስከፊ ዜናዎችን የማቅረብ ሱስና ፍላጎት ኖሮን ሳይሆን እንደ አለመታደል ሆኖ በአገራችን ሰማይ ላይ ያንዣበበ አደጋና በመሬቷ ላይ የማያልቅ የመከራ ማሳ የሰፈነ በመሆኑ ነው።ደስታና ሰላም ፣የሕዝብ እርካታና የአገር አንድነት የሰፈነባት አገር ብትኖረንማ ኖሮ እኛም የዚያው አወዳሽና ተቋዳሽ ለመሆን በበቃን ነበር።አሁን ግን የምንጋራው የመከራ ዘመን በመሆኑ ከዚያ እውነታ ሳንርቅ መከራው እንዲወገድና ለተሻለች አገር የሚቻለንን ከማበርከት ወደኋላ አንልም። ከሁሉም መጀመሪያ በሽታውን የደበቀ መድሃኒት አይገኝለትም ስለሆነ ውስጣችንን በመፈተሽ ጠንካራና ደካማ ጎናችንን አውቀን ሁሉም አገር ወዳድ መፍትሔ እንዲፈልግ ጥሪ ከማድረግ ሌላ የተሻለ አማራጭ የለንም። ለዚያም ነው ያለውን በገሃድ የሚታይ ሃቅ ሳንሸፋፍንና ሳንፈራ ለማቅረብ የምንሞክረው።

በወራሪዎችና በአገር አፍራሽ በሆነ በጎሰኞች ሥርዓት የተከፋፈለ አገርና ሕዝብ ለአንድነት፣ ለሰላምና ለእድገት ያልታደለ ለመሆኑ በተመሳሳይ ችግር ተዘፍቀው የነበሩት አገሮች የገጠማቸውን የመጨረሻቸው እጣ ፈንታ ምን እንደሆነ ማወቅና ማሰቡ ከገባንበትና ወደፊትም ልንገባበት ከምንችለው ማጥ ለመውጣት የምንችልበትን መንገድ ለመፈለግ ይረዳናል።አሁን ያለንበትን ደረጃ ስናጤነው አስቸኳይ መፍትሔ ካላገኘንለት በቀር የእኛም አገር መዳረሻ ወደ ዚያው የሚያመራ መሆኑን ነው።ባለፉት 30 ዓመታት የሰፈነው የጎሰኞች ሥርዓት አሁን ላለንበት ኑሮ፣ለእርስ በርስ ግጭትና ለመበታተን ስጋት ዳርጎናል።ይህ ስርዓት ካልተወገደ በስተቀር የነገው እጣፈንታችን ከበፊቱና ከእስካሁኑ የባሰ እንደሚሆን በእርግጠኛነት መናገር ይቻላል።

ምንም እንኳን ይህንን አደጋ የተረዱ ጥቂት አገር ወዳዶች ትግል ቢያደርጉም ሥርዓቱን ለመለወጥ የሚችል ጠንካራ ሕዝባዊ ሃይል ባለመፈጠሩ ምክንያት ትግሉ መና እዬሆነ መስዋእት ከመክፈል ሌላ ያመጣው አመርቂ ለውጥ የለም።ሕዝባዊ ጠንካራ ሃይል ስንል ግን ሕዝቡ አልታገለም ማለታችን አይደለም። በተበታተነም መልኩ ቢሆን ታግሏል፤ብዙም መስዋዕት ከፍሏል።ግን ለሚፈልገው ለውጥ አልበቃም ማለታችን ነው። አሁንም ይታገላል፣በዬቦታውም ብዙ መስዋዕት እየከፈለ ነው።የሚያደርገው ትግል ግን እንደ ትናንቱ ዛሬም በተበታተነ መልኩ ነው። ወደፊትም ቢሆን ከዚያ ተመሳሳይ ድግምግሚት ወይም አዙሪት ካልወጣና የትግሉን አቅጣጫ በቅጡ የሚመራ አካል ካልተፈጠረ የለውጥ ባለቤት ሊሆን አይችልም።መሪ መኖሩም ብቻ ሳይሆን የሚመሩበት ራዕይና መርህ መንደፍ ለውጤቱ ወሳኝ ነው።ውድቀትም ሆነ ስኬት ምክንያት ይኖረዋልና ከሁሉም በፊት ላለመሳካቱ ምክንያት ይሆናሉ ያልናቸውን ለማሳዬት እንሞክራለን።

ከላይ እንደገለጽነው በሽታውን ያልተናገረ ወይም የደበቀ መድሃኒት አይገኝለትም።ስለሆነም በሽታችንን ሳንደብቅ መናገር ይኖርብናል።

እኛ ኢትዮጵያውያን በተለይም የአሁኑ ትውልድ የሰፈነውን የጎሳ ፖለቲካና ሥርዓት እንደ ዴሞክራሲ መብት በመቁጠራችን ለጎሰኝነት ትልቅ የወሳኝነት ሥልጣን ሰጥተናል።በጎሳ ተዋረድ ተከፋፍለናል፣እኛ ብቻ ሳንሆን መሬቱም በጎሳ መስመር ተከልሏል።ባሕልና እምነታችን የጎሳ ታፔላ ወይም መታወቂያ ሰሌዳ ተሸክሞ ጎራ ለይተን እርስ በርሳችን እንናቆራለን፤በጠላትነት ተፈራርጀን እንገዳደላለን።ችግራችን ሥርዓት ወለድ መሆኑ እዬታወቀ በዚያ ላይ ከመረባረብ ይልቅ፣አንዱ ንጹህ ዜጋ በሌላው ንጹህ ዜጋ

እንደተበደለ፣አድርገን በማሰብ በመሰል ወገናችን ላይ ጥላቻ ቋጥረን የበቀል እርምጃ እንወስዳለን። እራሳችንን በጠላትነት ዘርፍ ውስጥ ፈርጀን፣እኛው በራሳችን ላመጣነው ችግር መፍትሔ እንዲሰጡን የውጭ ሃይሎችን እንማጸናለን።ከመካከላችን የወጡ ጥቂት አስተዋዮች ቢኖሩ የሚሉትን ከመስማት ይልቅ በባእዳን አምልኮ ተተብትበናል።ወገን ከሚሰጠን ማር ይልቅ ጠላት የሚግተን ኮሶ ይጥመናል። የራሳችን የሆነውን ቅን አሳቢና አሳሳቢ ከመከተል ይልቅ አጋልጦ መስጠት፣መክዳትና መከዳዳት አንዱ ልማዳችን ነው። ለሰላም ጥሪ ከሚያደርገው ቀና ዜጋ ይልቅ የጎሳችን ተወላጅ የሆነ መናጢና ክፉ ለሚያሰራጨው የጥፋት ጥሪ ዋጋና ትኩረት እንሰጣለን። የአላማ ጽናት ስለሚጎለን ለቆምንበት ዓላማ እስከመጨረሻው አንገፋበትም።በድርጅት ላይ ድርጅት መፍጠሩን እውቀት አድርገን ወስደናል። ወረተኞች ነን።ለመጣው ሁሉ እናጨበጭባለን።ቁም ወቃሽ ሟች አወዳሽ ሆነናል።የምንነዳው በእውቀት ሳይሆን በስማ በለው ፕሮፓጋንዳ ወይንም በጉልበት ላስገበረ ጨካኝ ቡድንና ግለሰብ ነው። ችግርና መፍትሔን ከጎጣችን ውጭ ይመጣል ወይም ይምጣ ብለን አናምንም።የሰፈሬ ጅብ ይብላኝ የሚለው አስተሳሰባችን ከመሰል ወገናችን ጋር አብረን እንዳንቆም አድርጎናል።ፖለቲካችን፣ ኤኮኖሚያችን፣ማህበራዊ ትስስራችን የሚነደፈው ከጎሳና ከጎጥ አመለካከታችን አኳያ ሆኗል።መደጋገፍን ሳይሆን መጠላለፍን እውቀትና ችሎታ አድርገን ወስደናል።ምቀኝነት አንዱ አብሮን የኖረ በሽታችን ነው።በበታችነት ስሜት እልህና በቀል ተሸከመን ሌላውን መሰል ዜጋ መጥላትን ወግና ልማዳችን አድርገነዋል።በአንዱ ጉዳትና ኪሳራ እኔ ልጠቀም፣ሌላው ሞቶ እኔ ልኑር የሚለው እራስ ወዳድነት ቀስፎ ይዞናል።ሌላውም እንደኛው የመኖር መብት እንዳለው አናውቅም።አገር የጋራና የሁሉም ዜጋ ንብረት መሆኗን ዘንግተናል።እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል በሚል ህሳቤ ለመጭው ትውልድ አናስብም፤ባለ አገር ሆኖ እንዲኖር አንጨነቅም። ልናወርሰው የምንሻው ቢኖር አገር አልባ ሆኖ በስደት ኑሮውን እንዲገፋ ነው።ወይም እርስ በራሱ እዬተላለቀ እንዲኖር የጥላቻ ትርክት እዬነገሩ ማሳደግ ነው።ለዚያ የሚረዳ ሃውልት ማቆም፣መጽሃፍም አዘጋጅቶ ማስተማር ነው።ሰፊ ለም መሬት፣በቂ ውሃ፣ መልካም አዬር ኖሮን ማምረት አልቻልንም።ከበረዷማና ከበረሃማ አገሮች የእህል እርዳታ ለማግኘት እጃችንን እንዘረጋለን።እርሃብና ስደት መታወቂያችን ሆኖ ለዓለም መሳቂያ መሳለቂያ ማስፈራሪያም ሆነናል።ያገኘነውን የብድርና የእርዳታ ገንዘብ ሳይቀር በአስረሽ ምችው ድግስና በውድ ተሽከርካሪ መኪና ግዢ፣በፎቅ ግንባታና ብልጭልጭ የቤት ዕቃ ወጭ እናባክናለን።ጊዜና ሃብታችንን የምናባክነው እርስ በርስ ለመጨራረስ በጎሳ ወታደራዊ ሃይል ግንባታና መሣሪያ ማካበት ላይ ነው።የተበደርነውን ገንዘብ መልሰን በጦር መሣሪያ ግዥ ለአበዳሪዎቹ እንሰጣለን።የሚተርፈን ወለድ መክፈልና መተላለቅ ብቻ ነው።ሁላችንንም የሚያስተሳስር፣ አንድ ነባርና ከቀድሞ ትውልድ የተረከብነውን በዓለም መድረክም ላይ ሲውለበለብ የኖረ ታሪካዊ፣ሌላው አገር የነጻነት ምልክት አድርጎ የተቀበለውን አረንጓዴ፣ቢጫና ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ጠልተን የተለያዬ ቀለም ያለው ባንዲራ ማውለብለብ መርጠናል፣ከአንድ ብሔራዊ መዝሙር ይልቅ የተለያዩ መዝሙሮች ማቀንቀን የክብርና እኩልነት መግለጫ አድርገን ወስደናል። ቋንቋ መግባቢያ መሆኑ ሲታወቅ ለዘመናት በዬትኛውም ቦታ ሄደን ከነዋሪው ሕዝብ ጋር የምንግባባበትን፣በአፍሪካ ብቸኛ ፊደል ያለውን የአማርኛ ቋንቋ ጠልተን በሰፈርና በጎሳ ቋንቋችን በመናገር ከክልላችን ውጭ ካለው ጋር አለመግባባትን፣በባዕዳን ፊደል በመጠቀም ኢትዮጵያዊነታችንን አሳልፈን ሰጥተን ባርነትን መርጠናል። ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል በሚል ስንኩል እምነት በሥልጣን ላይ መባለግን፣መዝረፍና ሙስናን እውቀትና ችሎታ አድርገናል።ከአገር እዬሰረቁ በውጭ አገር ባንክ ማካበትን ብልህነት አድርገናል።ወንጀለኛን ደፋርና ጀግና በማድረግ ዋሻና መከታ ሆነናል።ለፍትሕ ተባባሪ ከመሆን ይልቅ ለጎሳችን ወንጀለኛ ተባባሪ መሆንን መርጠናል።ሌላም ብዙ ድክመቶችን እናስተናግዳለን ስለሆነም ኑሯችንን ከድጡ ወደማጡ ፣ህይወታችንንም ተስፋ ቢስ አድርጎታል።

ከዚህ ሁሉ ድክመትና በሽታ እንዴት እንላቀቅ የሚለው ጥያቄ መመለስ አለበት።

ሁሉም ኢትዮጵያዊ በሰው ልጅነቱ ፣በአንድ አገር ዜግነቱ ማመን አለበት።ከቀደሙት አባቶቹ የተረከባትን አንድ ኢትዮጵያ ለሚመጣው ትውልድ የማስረከብ ግዴታ እንዳለበት ማወቅ አለበት። ኢትዮጵያ ለሁሉም የምትበቃ አገር መሆኗን አምኖ በጋራ ኑሮውን ለማሻሻል የሚችልበትን ሥርዓት ለማስፈን ጥረት ሊያደርግ ይገባል። ለኑሮ ክብደትና መከራ፣ለሰላም እጦቱና ለስደቱ የዳረገው ኢትዮጵያዊ መሆኑ ሳይሆን በኢትዮጵያ ውስጥ እትዮጵያዊ የሆነ ሥርዓትና መንግሥት አለመኖሩ ነው። በንትርክና በመከፋፈል ብሎም እርስ በርስ በመጋጨትና በመገዳደል ችግርንና ድህነትን ብሎም ኋላ ቀርነትን ማሶገድ አይቻልም።ከባዕዳን ይልቅ ያገሩ ዜጋ የሚያስተማምን አጋሩ መሆኑን አምኖ መቀበል ይገባል። ከሠራንባት አገራችን ሃብታምና በቂ ነች።የአፄር ንብረቷ፣የተፈጥሮ ሃብቷ፣ውሃና ፣ለም አፈሯ፣ ከሌሎቹ ብዙ አገሮች የተሻለ ነው። አገር ወዳድ መንግሥትና ሥርዓት ቢሰፍን ከራሷ አልፋ ለሌሎቹ መትረፍ ትችላለች። የምትከበር እንጂ የምትናቅና የምትጠላ አገር አትሆንም።ስደተኞችን የምታስተናግድ እንጂ ልጆቿን የምታሰድድ አገር አትሆንም።ስለሆነም በጥላቻ የተነደፈው ትርክትና በነሳ ተራ የተዋቀረው በባዕዳን ሴራ የተነደፈው ሥርዓት መወገዱ አሁን ያለውን መጠነ ሰፊ ችግር ያሶግዳል፣የቁልቁለቱን መንገድ ያስተካክላል።ዜጋ በፈለገው ቦታ ሄዶ ለመኖር፣ለመሥራትና ሃብት ለማትረፍ ፣ከወደዳትና ከወደደችው ጋር ተጋብቶ ወልዶ ተዋልዶ ለመኖር ሰብአዊና ዜጋዊ መብቱን ያረጋግጥለታል።ብንተባበር አገራችን እንድትፈርስ የሚጥሩ፣ድንጋይ የሚያቀብሉና የሚቋምጡ ቢኖሩ ቅስማቸው ይሰበራል።

ስለሆነም በዬአቅጣጫው ተበታትኖ የሚሰማው ብሶት፣እልህና ብስጭት የሚቀሰቅሰው እምቢ ባይነት በአንድ በተደራጀና በአማከለ መልኩ መሆን ይኖርበታል።ይህ ከሆነ በዬአቅጣጫው የሚጠፋው የሰው ህይወት፣ የሚባክነው የአገር ሃብትና ቅርስ ይድናል።የሰው ሃይልና ገንዘብ በአስፈላጊው ቦታ ውሎ የሚፈልጉትን ለውጥ ለማምጣት ያስችላል።በስነሥርዓት ና አንድ ቋሚ አመራር ባለው የጋራ ግንባር የሚመራ ሕዝባዊ ትግል ለስርዓተ አልበኞችና ግላዊ ፍላጎት ላላቸው እራስ ወዳዶች፣ብሎም ከፋፋዮች፣ለነሰኞችና ነጠኞች የሚመች አይሆንም።የነሱንም ግብአተ መሬት የሚያቀርብ ይሆናል።

ከላይ ድክመታችንንና ለድክመታችንም መፍትሔ የሚሆኑ ሃሳቦችን በአጭሩ ለማቅረብ ሞክረናል። ቅንነት ካለ ሃሳቦቹን ተቀብሎ በተግባር መተርጎም ይቻላል።ያ ከሆነ ደግሞ መጥፎ ዜናና መርዶ የምናሰማበት ምክንያት አይኖርም፤የደስታና የምስራች ዜናዎችን የምንጋራበትን መድረክ የምናዘጋጅ ይሆናል።ያ እስኪሆን ድረስ ግን ያለውን ተጨባጭ ከመግለጽ ወደኋላ አንልም፤ ስለሆነም የሰሞኑን ልብ የሚሰብር ሁኔታ ለማቅረብ እንገደዳለን። ችግርን ማወቅ ለመፍትሔው መንደርደሪያ ይሆናል ብለን እናምናለን።ችግሩን መደበቅ የባሰ ችግር እንዲመጣ ወይም ችግር ቤተሰብ ሆኖ ተለምዶ እንዲኖር ማድረግ ይሆናል።ማጋለጥና መቃወም ተገቢ ነው።

በአለፈው እሑድ ባስተላለፍነው የዜና ክፍለጊዜ በኢቃቂ ክፍለከተማ በፕሮቴስታንትና በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች መካከል በተነሳው ውዝግብ የአንድ ወጣት ኦርቶዶክሳዊ ህይወት ማለፉን ዘግበን ነበር።ግጭቱ የተቀሰቀሰው መንግሥት ሆን ብሎ በክርስትና እምነት ተከታዮች መካከል ጥላቻና ግጭት እንዲፈጠር ካለው ፍላጎት በመነጨ የቦታ ድርሻ ጭቅጭቅ በመነሳቱ ነው።በዚህ ንትርክ የከባቢው የፖሊስ ሃይል ጣልቃ ገብቶ በወሰደው ወገንተኝነትን ባንጸባረቀ የሃይል እርምጃ በጥይት ተመቶ ህይወቱ ያለፈው ዘመድኩን አማረ የተባለ የ22 ዓመት ወጣት ሲሆን ድርጊቱ ብዙዎችን ከማሳዘኑም በላይ አስቆጥቷል። የቀብር ስነስርዓት ለማካሄድ ቤተሰቡና ምእመናን ሲዘጋጁ ፖሊስ አስከሬን በመቀማትና በመከልከል ከግድያው በላይ ልብ የሚሰብር ድርጊት የፈጸመ ቢሆንም ከብዙ ትግልና ጭቅጭቅ በኋላ እንደ ቤተሰቡ ፍላጎት የቀብር ስርዓቱ እሮብ እለት መጋቢት 28 ቀን 2014 ዓም ብዙ

ምእመናን በተገኙበት ተፈጽሟል።ጽናትና ብርታቱን ለቤተሰቡ፣ለጓደኞቹና ለመላው የኦርቶዶክስ ምእመናን ሁሉ እንመኛለን።ገዳዩ ፖሊስና አስገዳዩ አካል ለፍርድ እንዲቀርቡም እንጠይቃለን።ለሟች ቤተሰቦችም መንግሥት ካሳ እንዲከፍልና ለወደፊቱም ከመሰል ተግባር እንዲታገድ እንጠይቃለን። እውነተኛ የፕሮቴስታንቱ እምነት ተከታዮች ወገኖቻችን የክርስቶስን መንገድ በሚቃረን መልኩ፣ የእምነት ተቋማቸውን ምሽግና ከለላ በማድረግ በስማቸው የሚደረገውን የጎሳ ተኮር ጥላቻና የፖለቲከኞችን ጥቅም ለማስጠበቅ በሚረዳ መልኩ በተረኝነት እብሪት የተሰለፉትን ግብረ ሰይጣናት ሊያወግዙ ይገባል እንላለን።እምነታቸውን በነጻነት ሊከተሉ የሚችሉት ነጻ ኢትዮጵያ ስትኖር ነውና ለነጻና ዴሞክራቲክ ኢትዮጵያ ከሌላው እምነት ተከታይ ወገናቸው ጋር በመቆም መታገል ይኖርባቸዋል።በተጠቃሚነት መንፈስ የሚፈጸም ጥፋት ነገ ጸጸትን ይወልዳልና ቆም ብለው እንዲያስቡበት እንመክራለን።በጎሰኝነት ልክፍት ሳይለከፉ የዬሱስ ክርስቶስን አስተምሮ የሚከተሉ፣ ለሰው ልጆች ክብርና ለአገር አንድነት የቆሙትን የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ክብር ምስጋና ይድረሳችሁ እንላለን።

ከዚሁ ከአዲስ አበባ ሳንወጣ ሰኞ መጋቢት 26 ቀን 2014 ዓም ለሚ ኩራ በተባለው አካባቢ በሚገኝ ትምህርት ቤት ውስጥ የሙስሊም ተማሪዎች ባነሱት የመስገጃ ቦታና ጊዜ ጥያቄ ፖሊስ ከባቢውን በተኩስ ሲንጠው ማምሸቱ ታውቋል።የሞተ መኖሩ ባይታወቅም እንደ ተኩሱ ድምጽና ብዛት ከሆነ ግን ብዙ ጉዳተኞች ሊኖሩ ይችላሉ የሚል ግምት አለ። በድብደባ የቆሰሉ መኖራቸው ታውቋል።የሕዝብን ጥያቄ በአግባቡ መመለስ የማይፈልገው ብቻ ሳይሆን የማይችለው የኦሮሙማው ተረኛ መንግሥት የዚህ አይነቱ እርምጃ የማንንቱና የችሎታው መግለጫ ከሆነ ውሎ አድሯል።ከዚህ የተሻለም መንገድ ይከተላል ተብሎ አይጠበቅም።ሆን ተብሎ በመንግሥት አካላት የተጠነሰሰ ሴራ ከጀርባው አለ የሚልም ጭምጭምታ ይሰማል። በንጉሥ ሃይለሥላሴ ዘመን በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች በሮመዳን ጾም ጊዜ ሙስሊም ተማሪዎች በእረፍት ሰዓት የመስገድ ነጻነት ነበራቸው።በትምህርት ቤቱ አዳራሽ ወይም ጸጥ ባለ ቦታ ይሰግዱ እንደነበር በህይወት ያሉና የሚያውቁ ይመሰክራሉ።የመጽሃፍ ቅዱስ ክለብም የነበራቸው ትምህርት ቤቶች ነበሩ።ሆኖም ግን እንደ አሁኑ ሃይማኖት የሚለያዩበት ሳይሆን ተከባብረውና አንዱ ለሌላው አስቦ የኖሩበት ጊዜ ነበር። አሁንም ቀና ልብ ቢኖር ኖሮ በመስገጃ ቦታ ግርግር ሊፈጠር አይችልም ነበር፤በቀላሉ የሚፈታ ጥያቄ ነው። ተማሪው ግፋ ቢል ሃይማኖቱ ከሚያስገድደው በቀን የአምስት ጊዜ ሶላት በትምህርት ቤት ባለበት ሰዓት አንድ ጊዜ ቢሰግድ ጉዳት አይኖረውም።ቀኑን ሙሉ ትምህርት አቋርጬ ልስገድ የሚል ይኖራል ተብሎ አይታሰብም።የትምህርት ቤቱ አስተዳደር የሰጠው ምክንያት ትምህርት ቤት ውስጥ ሃይማኖት ተኮር እንቅስቃሴ ማድረግ ተገቢ አይደለም የሚለውን ብንጋራም ያለውን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት በአጭሩ ሊቀጭ የሚችልበትን መንገድ መፈለጉ የተሻለ ነበር።ለአንድ ወር የሮመዳን ጾም ለሚከታተሉት ተማሪዎች ልዩ መመሪያ ቢወጣ የተሻለ ነው እንላለን።የተማሪዎቹን ተቃውሞ በመደገፍ አርብ እለት የጁምአን ስግደት ተከትሎ በመርካቶ የተጀመረው የሙስሊሞች ተቃውሞ በመላ አገሪቱ በመቀጣጠል ላይ ነው።በሶላት አንደራደርme!bfeትሕ ለሙስሊም ተማሪዎች የሚለው መፈክርም እያስተጋባ ነው።በፍጥነት መልስ ካልተሰጠው ወደ አስከፊ ደረጃ ሊያመራ ይችላል የሚል ስጋት አለን። የንጹህ ሙስሊም ጾመኛ ተማሪውን ጥያቄ በመጠቀም ወደ አላስፈላጊ ግጭት እንዲያመራ የሚፈልጉ የመንግሥት አካላትና የውጭ ተላላኪ ቡድኖች ስለማይጠፉ በንቃት መከታተል የሁሉም ደግ አሳቢ ሙስሊምና ክርስቲያን ተግባር ነው።በትምህርት ቤት ውስጥ መጽሃፍ ቅዱስ ልስበክ ወይም ቁርዓን ላስተምር የሚል ካለ ትምህርት ቤቶች ለዚያ ተገቢ ቦታዎች አይደሉም።ለየእምነቱ ትምህርት ለክርስቲያኑም ቤተክርስቲያን፣ ለሙስሊሙም መስጊድ ተገቢ ቦታዎች ናቸው።

ባለፈው እሁድ በአማራው መኖሪያ በሰሜን ሸዋ ምስራቅ  በሸንኮራ ልዩ ስሙ አውራመንገድ በተባለ ቀበሌ የሥርዓቱ ታጣቂ በኦነግ ሸኔ ስም  ባደረገው ወረራ የከባቢው ኑዋሪ የመጣውን ሃይል ተቋቁሞ በመመለሱ የተበሳጨው የኦሮሞ ክልል መንግሥት  ነኝ ባይ የአማራው አክራሪ ጽንፈኛ የኦሮሞን መሬት ወሮ ጉዳት አድርሷል የሚል ውንጀላና ዛቻ የታጨቀበት መግለጫ አውጥቷል።ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሃል እንደሚባለው በገዛ ቤቱ አርፎ በሰላም የተቀመጠውን ሕዝብ አፈናቅሎ መሬቱን ወሮ ለመያዝ የተደረገ የከሸፈ ሙከራ መሆኑን ታዛቢዎች የሚመሰክሩት ሲሆን የተጠቀሰው ቦታም የአማራው ማህበረሰብ መኖሪያ የነበረ ለመሆኑ ታሪክ ያረጋግጣል። የኦሮሙማው አስተዳደር እራሱ መልምሎና አስታጥቆ የላከው አሸባሪ በፈጸመው ወንጀል ሌላውን ተጠያቂ አድርጓል።ሙከራውም ሆነ መግለጫው ጠብ ያለሽ በዳቦ ከሚል ተንኳሽነት የተለዬ አይደለም፤ስለሆነም ለቀጣዩ ጥቃት አማራው በንቃት ተዘጋጅቶ መጠበቅ ይኖርበታል።በዚሁ የሸዋ ክፍለሃገር ወደ ደራ የሚወስደው መንገድ በመንግሥት ድጋፍ በሚንቀሳቀሰው ኦነግ ታጣቂ ተዘግቶ ሕዝቡ መግቢያና መውጭያ ማጣቱ ታውቋል።ይህ ቦታ ወደ ሰሜን ሸዋ፣ወሎና ጎጃም ለመሄድ መሃል ላይ የሚገኝ ነው።ይህንን ቦታ መቆጣጠር ለኦሮሙማው ተስፋፊ ወሳኝ እስትራተጂክ መንደርደሪያ ነው።መንግሥት ተብዬውም በይፋ ለኦነግ ወታደራዊ ማሰልጠኛ እንዲሆን የፈቀደው ቦታ ነው።

ገንዶ ራቻ አሙማ በተባለ ቀበሌ ኦነግ አማርኛ የተጻፈባቸውን ሰሌዳዎችን ዬቀደደ በመጣል፣የኦነግን ባንዲራ እዬተከለና ሕዝቡን እያስገደደ ግብር በመሰብሰብ ላይ መሆኑ ይፋ ሆኗል። በምስራቅ ወለጋ ኪራም ወረዳም  አዲስ ዓለም በተባለ ቀበሌ የመከላከያና የከባቢው  አስተዳደር በጥምረት የአማራ ተወላጆች የሆኑትን ነጥሎ እንዲሰበሰቡ በማድረግ ትጥቃቸውን በማስፈታት እንደ ሸኔ አሸባሪዎች ናቸው በማለት ፈርጆ ለጥቃት ዳርጓቸዋል።

አዲስ አበባን ለመውረር ኦነግ ተከታዮቹን አሰማርቶ መንደሮችንና መግቢያ መውጫ በሮችን ሲያስጠና፣ ወራሪ ቡድኖችንም ለማሰማራት ስልጠና ሲሰጥ መክረሙ በማስረጃ ቀርቧል።ኑዋሪውን እያባረሩ የኦሮሙማ መስሪያ ቤቶች ግንባታ የነገዋ አዲስ አበባ ምን ልትሆን እንደምትችል አመላካች ነው።ዝም ተብሎ መታለፍ የለበትም፤ ነዋሪው እራሱን ለማዳን ድርጅታዊ  በቂ ዝግጅት ማድረግ ይኖርበታል።

በሲዳማ ክልልም የኦሮሙማው ትንኮሳ ቀጥሏል። በቦረናም እንዲሁ ።በደቡብ  ክልልም በጉራጌ ዞንና በጉጂ አማሮ ወረዳ የሚኖሩትን ለማፈናቀልና መሬታቸውን ለመንጠቅ ጦርነት ከፍቷል።እንደ አበደ ውሻ ሁሉንም በመንከስ እስፋፋለሁ ብሎ ያቀደው ጠባብ የኦሮሙማው ቡድን ለድፍረቱ  ማስታገሻ ካልተገኘለት በቀር የሚመለስ አልሆነም።በቋሚነት ሊቆጣጠር የሚችል ባይሆንም ከማውደም አይመለስም። በሰሜኑና በምዕራቡ፣በደቡብና ቤንሻንጉል በመሃል አገር ሸዋና ወሎ፣በጎጃም የሚረጨው መርዝ መምከን አለበት።ሊያመክን የሚችለውም የኢትዮጵያውያን የተባበረ ክንድ ብቻ ነው።

የወያኔም ወረራ ተጠናክሮ ቀጥሏል። በሰሜን ወሎ  የራያና አዘቦን መሬት እንደያዘ ሲሆን ወልቃይትና ጠገሌንም ለማስለቀቅ በከባድ መሣሪያ የታገዘ ብዙ ጦር አሰልፎ ሙከራ በማድረግ ላይ ነው።ላቀደው ወረራ በሱዳን በኩል ብዙ መሣሪያ ማግኘቱ ይፋ ሆኗል።በአፋርም በኩል ጦሩን አጠናክሮ ተደጋጋሚ ሙከራ አድርጓል።የአፋር ሕዝብና ልዩ ሃይል ከመንግሥት ተብዬው በኩል እርዳታ ባያገኝም የመጣበትን የወያኔ ወራሪ እንደለመደው ገርፎ መልሶታል።አሁንም እዬተፋለመ ነው።በቂ እርዳታ ካላገኘ በስተቀር ብቻውን ለመቋቋም የመሣሪያውም ሆነ የስንቁ አቅርቦት  መጓደል ለችንፈት ይዳርገው ይሆናል። ስለሆነም ሁሉም ኢትዮጵያዊ በተለይም የአማራው ማህበረሰብ ከአጋሩ ከአፋር ሕዝብ ጎን ሊሰለፍ ይገባዋል።

ለወያኔ የሚደረገው የምዕራባውያን የፖለቲካና የጦር መሣሪያ ድጋፍ አሁንም ቀጥሏል። በእርዳታ ስም በመኪናና በአውሮፕላን መሣሪያ ማጓጓዛቸው በተጨባጭ ማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን በተጨማሪ ሰሞኑን የአምነስቲ ኢንተርናሽናልና የሁማን ራይትስ ዋች ያወጡት ጥምር መግለጫ የምዕራባውያንን አቋምና ፍላጎት የሚያሳይ ነው።በሰብአዊ መብት ጥሰት ስም የወጣው መግለጫ ወልቃይትንና ራያን የምዕራብ ትግራይ በማለት እውቅና የሰጠ ሲሆን በወያኔ የተፈጸመውን የሰብአዊ መብት ጥሰትና የዘር ማጥፋት ወንጀል በአማራው ላይ ለመደፍደፍ ሞክሯል።ወትሮስ የአድዋ ተወላጅና የወያኔ አባል የሆነው የአምነስቲ ቃል አቀባይ ከሚያጠናክረው ዘገባ ምን ይጠበቃል? ቴዎድሮስ አድሃኖም በዓለም ጤና ድርጅት በኩል ከሚያካሂደው ወገንተኝነት ዘመቻ ጋር ተመሳሳይና የተያያዘ ነው።ሆኖም ግን የትም ሆነ በማንም በሰብአዊ ፍጡር ላይ የሚደርስ ጉዳት መጋለጥና መወገዝ አለበት፤ተጠያቂ የሆነም አካል ሊጠዬቅ ይገባል።የሰብአዊ መብት ጥሰት በፖለቲካ ጥቅምና አቋም አንጻር መታዬት የለበትም። ምዕራባውያን መንግሥታት በራሳቸውና በነሱ ደጋፊ በኩል የሚፈጸም የሰብአዊ መብት ጥሰት አይቆረቆራቸውም።ተገቢና ትክክል መሆኑንም ያምናሉ።

የነአምነስቲ መግለጫ መቅረቡ ተገቢ ነው።ሁል ጊዜ ትክክለኛ ወይም ስህተተኛ መግለጫ ያንጸባርቃሉ ማለት አይቻልም፤ ለዚያም ነው አምነስቲ በሦስት መልክ ማለትም ጥሩ፣መጥፎና አስቀያሚ (Good,Bad and Ugly)በሚል ደረጃ የሚገለጸው። አሁን በኢትዮጵያ ዙሪያ ያወጣውን መግለጫ ጥርጣሬ ውስጥ ያስገባው በጎንደር ዩኒቨርሲቲ ተካሂዶ የወጣውን የምርመራ ውጤት ተከትሎ የወጣ በመሆኑ ሲሆን እሩጫው በወያኔ ላይ ሊቀርብ የሚችለውን የወንጀል ክስ ለማጨናገፍ ወይም ለመሸፋፈን እንደሆነ ብዞዎች ይናገራሉ። በተጨማሪም የአሜሪካንን የእቀባ እረቂቅ ተግባራዊ ለማድረግ የሕግ ሽፋን ለመስጠት የታሰበ መሆኑም ከሚካሄደው ሴራ አንጻር የሚያዩ አልጠፉም።የእኛም እይታ ከዚያ የራቀ አይደለም።

በዩኒቨርሲቲው የረጅም ጊዜ ጥናትና ምርምር በሽዎች የሚቆጠሩ የወልቃይትና ጠገሌ እንዲሁም የራያና አዘቦ ነዋሪ የሆኑ አማራዎች ተጨፍጭፈው መገደላቸውን የሚያሳይ የጅምላ መቃብር ቁፋሮና የሰው ምስክር ቃል ተጠናቅሮ የቀረበውን ማስረጃ ለመከላከል ሲባል የተዘጋጀ መግለጫ ነው የሚለው ቀልብ የሚስብ ሆኗል።ከዚህ ቀደም በወያኔ በማይካድራ የተፈጸመውን ጭፍጨፋ በማጋለጥ በትግራይ ውስጥ ግን ምንም አይነት ጭፍጨፋ(ጄኖሳይድ) እንዳልተፈጸመ ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ ጋር ያወጣው መግለጫ ያመለክታል።የምዕራብያውያኑን የልብ ትርታ እያዳመጠ የሚንቀሳቀሰው አምነስቲና ሁማን ራይትስ ዋች ቢደግፉም ቢነቅፉም አለቆቻቸውን ለማስደሰት እንጂ ለሕዝብ አስበው የሚያደርጉት ስላልሆነ በነሱ ላይ መተማመን ተገቢና አስፈላጊ አይሆንም።ኢትዮጵያውያን በራሳችን አጣሪ፣በራሳችን የፍትሕ መንገድ መመካት ይኖርብናል።የዚያ ባለቤቶች ብንሆን ኖሮ ወንጀሉም ላይፈጠር ይችል ነበር።

የኦሮሙማው ተረኛ ቡድንም እስከ አሁን ድረስ በተለይም ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ የፈጸመውና እዬፈጸመ ያለው የዘር ማጥፋት ወንጀል እንዳይጋለጥበት ብዙ ሙከራ እንደሚያደርግና ጥፋቱን ሁሉ በተቃዋሚው በተለይም በአማራው ማህበረሰብ ላይ ከመደፍደፍ እንደማይመለስ እሙን ነው።ለዚያም በሸንኮራ አካባቢ ያደረገውን ወረራ በአማራው ማህበረሰብ ላይ መደፍደፉ ማሳያ ነው።

በሁሉም አቅጣጫ መልካም ነገር አይሰማም፣አይታይም።ሰሞኑን በሶማሊያ ክልል ሁከትና ግርግር የታዬበት ነበር።በኑሮ ውድነትና በችግር የሚቆላው ሕዝብ ትግዕስቱን ጨርሶ የመንግሥት መጋዘን ሰብሮ በመግባት የተከማቼ እህል ዘርፏል።የራበው ሕዝብ መዝረፍ ብቻ ሳይሆን መሪዎቹንም ይበላል። የሚቀጥለውም እርምጃ ወደዚያ የሚያመራ ላለመሆኑ ዋስትና የለም።

ሌላው የሚገርመው የሰሞኑ ድራማ የኦሮሞ ኮንግሬስ ሊቀመንበር የሆነው መረራ ጉዲና በዚህ ግርግር ውስጥ ለአገር አንድነት አሳቢና ተቆርቋሪ መስሎ ብቅ ማለቱ ነው።የአኖሌን ሃውልት እንደ ታሪክ ማስረጃ አድርጎ የሚቆጥረው መረራ፣ምንሊክን እንደ አውሬ የሚቆጥረው መረራ፣ ለአገር አንድነት አሳቢ መስሎ ሲቀርብ ሰው ምን ይለኛል የሚል ግምት አላደረበትም።እውነት ለአገር አንድነት የሚያስብ ከሆነ የጎሳ ፖለቲካን መቃወም፤እራሱም የሚመራው ድርጅት ከጎሳ ማንነት ስያሜ በማራቅ በኢትዮጵያዊነት ተርታ በፖለቲካ ርዩተዓለም አኳያ እንዲሰለፍ ማድረግ፤ኢትዮጵያ የረጅም ዘመን ታሪክ ባለቤት መሆኗን መቀበል፤በኢትዮጵያዊነት ማመን፤ሁሉም ኢትዮጵያዊ በሥርዓቶቹ እኩል የተጎዳ መሆኑን ማመንና ማስተማር፣አንዱ ጎሳ ከሌላው ጎሳ የተለዬ ጥቅም እንዳልነበረው፣ሁሉም ጎሳ በራሱ ጎሳ ጉልበተኞች ተረግጦ እንደኖረ መመስከር፤ሁሉም ዜጋ በፈለገው ቦታ ሄዶ የመኖርና ንብረት የማፍራት መብቱ መከበር እንዳለበት፣ባሕልና እምነቱንም መከተል እንደሚችል በግልጽ መናገር ይኖርበታል።ከዚያም አልፎ በወለጋ፣በቤንሻንጉል፣በከሚሴና አጣዬ፣በሻሼመኔ፣በአምቦ፤በቡራዩ...ወዘተ ሕይወት ያጠፉ የኦሮሞ አሸባሪዎችና ዘራፊዎች ለፍርድ እንዲቀርቡ መጠዬቅ ይኖርበታል።ወያኔም በፈጸመውና በመፈጸም ላይ ያለውን ወንጀል መኮነንና ማውገዝ ተገቢ ነው።በመረራ በኩል ግን የቀረበው ሃሳብ ወንጀለኞቹ የሰላም ውይይቱ አካል ይሁኑ፣በሕግ አይጠዬቁ የሚል ነው።ይህ ለእውነተኛና ፍትሃዊ መፍትሄ ከማሰብ የመነጨ ቅን ሃሳብ አይደለም።

የመረራ ጉዴና አፌኮም ሆነ የዳውድ ኢብሳ ኦነግ፣የአብይ አህመድ ብልጽግናም ሆነ የሌንጮ ባቲ ኦዴድ ያላቸው ልዩነት በሥልጣን ከፍፍሉ ላይ እንጂ ኢትዮጵያን በማፍረሱ ጥያቄ ላይ አይደለም። አንዱ ከሌላው የተሻለ ለኢትዮጵያ በተለይም ለአማራው ማህበረሰብ ፍቅር የለውም።ስለዴሞክራሲና ፍትሕም አይጨነቁም፣ደንታቸው አይደለም።ለነሱ ዴሞክራሲና ፍትህ ማለት ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የሚቃወም ሃይል በነጻ ያሻውን እንዲያደርግና እንዲያገኝ መፍቀድ ማለት ነው።ለነሱ አንዱና ብቼኛው የጋራ መግባቢያቸው በሃሳብ ካርታ ላይ የነደፉት ኦሮሚያ የተባለ በታሪክ ኖሮ የማያውቅ በሌላው ኪሳራ አገር መመሥረት ነው።

ሁሉም የኦሮሞ ተወላጅ ይህንን እኩይ ዓላማ ይቀበለዋል ብለን አናምንም።ባለመቀበሉም ብዙ የኦሮሞ ተወላጅ በጸና ኢትዮጵያዊነት አቋሙና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ በመሆኑ በግፍ ተጨፍጭፏል።ወደፊትም ከመጨፍጨፍ አይድንም።ለሱም ያለው ብቸኛ አማራጭ እንደ አደዋው ዘመቻ ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ጋር ተባብሮ መታገል ነው።ይህንን የጎሳ ስርዓትና የአፓርታይድ የክልል አወቃቀር ከነ ሕገ ጎሳው ማሶገድ ነው።

ለወሳኙ ትግል ሁሉም ተባብሮ ይነሳ!!የጋራ አስተባባሪ አካል ይቋቋም! የሚቋቋምበት የጋራ መርህ

1/ በኢትዮጵያዊነት ማመን

2/ በኢትዮጵያ አንድነትና የዳር ድንበር መከበር ላይ የጸና አቋም መከተል

3/ የጎሳ ፖለቲካና የክልል አወቃቀር ከነሕገ ጎሳው እንዲወገድ የማያወላውል እምነት መያዝ

በነዚህ አንኳር ዓላማዎች ላይ የተመሠረተው ሕዝባዊ ሃይል ከሚቀናቀኑት ጋር ታግሎ የማሸነፍ ዕድሉ ከፍተኛ ነው።ወታደራዊ ትግሉን ከመምራቱም ጋር አያይዞ ለፖለቲካውና ለቀሪው ትግል ከላይ በተዘረዘሩት መስፈርቶች የሚስማሙ የፖለቲካ ፣ የሙያና የማህበረሰብ ድርጅቶች፣የሚካፈሉበት የሽግግር መንግሥት ማቋቋም አስፈላጊ ነው እንላለን።

ኢትዮጵያ ከጎሳና ከሃይማኖት በላይ ናት!!!